መልእክት አምስት

## ዕዝራ፣ ካህን ጸሐፊ
## እና የዕዝራዎች—
## የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ የሚያውቁ ሰዎች—አስፈላጊነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዕዝ. 7፡6፣ 11-12፣ 21፤ 8፡21-23፤
ነህ. 8፡1-9፣ 11-13፤ 12፡26

**I. ዕዝራ ካህንም ጸሐፊም ነበር፤ ከዚህም የተነሣ፣ የፊደል ጸሐፊ ሳይሆን ካህን ጸሐፊ ነበር—ዕዝ. 7፡6፣ 11-12፣ 21፤ ነህ. 8፡1-2፣ 8-9፣ 11-12፤ 12፡26፦**

ሀ. ካህን ከጌታ ጋር የተዋሐደ እና በጌታ የተሞላ ነው፤ ዕዝራ እንደዚህ ዓይነት ሰው ነበር—ዕዝ. 8፡21-23።

ለ. ዕዝራ በእግዚአብሔር የታመነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የነበረ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ የሚያውቅ እና የእግዚአብሔርን ልብ፣ የእግዚአብሔርን መሻቶች እና የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ የሚያውቅ ሰው ነበር—7፡6፣ 11-12፣ 21።

ሐ. እንደ ካህን ጸሐፊ፣ ከጌታ ጋር ያለማቋረጥ በመገናኘት ከጌታ ጋር አንድ ነበር—ነህ. 8፡1-2፣ 8-9፣ 11-12፤ 12፡26።

መ. ዕዝራ ምንም አዲስ ነገር አልተናገረም፤ የተናገረው ነገር ሙሴ የተናገረውን ነበር—ዕዝ. 7፡6፤ ነህ. 8፡14፤ 2 ጴጥ. 1፡12።

ሠ. ካህናቱ እና ሌዋውያኑ የሕጉን ቃል ይማሩ ዘንድ ወደ ዕዝራ ተሰበሰቡ፤ በነህምያ 8፡13 *ይማሩ* የሚለው ቃል ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉሙን መረዳትን ያመለክታል።

**II. እስራኤል የእግዚአብሔር ምስክር መሆን ትችል ዘንድ ዕዝራ የእስራኤልን ሕዝብ በሰማያዊ እውነቶች በማስተማር መልሶ አቀናበራቸው—ቁ. 1-3፣ 5-6፣ 8፣ 13-18፦**

ሀ. በእስራኤል ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ውጥን በምድር ላይ ምስክሩ እንዲሆኑ በመለኮት የተቀናበሩ ሕዝብ—በእግዚአብሔር ቃል መልሶ የተቀናበሩ ሕዝብ—ለማግኘት ነበር—ኢሳ. 49፡6፤ 60፡1-3፤ ቆላ. 3፡16።

ለ. ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ፣ የእስራኤል ሕዝብ የተወለዱት እና ያደጉት በባቢሎን ስለነበርና በቅንብራቸው ባቢሎናውያን ሆነው ስለነበር አሁንም የማይታዘዙ ነበሩ፦

1. የባቢሎናውያን ንጥረ-ነገር ወደ ውስጣቸው ተሠርቶ እና ወደ ማንነታቸው ውስጥ ተቀናብሮ ነበር—ዘካ. 3፡3-5።
2. የእስራኤል አገር ዜጋ ለመሆን ወደ አባቶቻቸው ምድር ከተመለሱ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ቃል መልሶ መቀናበር አስፈልጓቸው ነበር—ነህ. 8፡1-3፣ 5-6፣ 8፣ 13።

ሐ. የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእግዚአብሔር መሠረት ወደ ነበረው ባሕል፣ እግዚአብሔርን ወደ ገለጠው ባሕል ለማምጣት የማስተማር እና መልሶ የማቀናበር አስፈላጊነት ነበር፤ እንደዚህ ዓይነቱ ባሕል ትልቅ ትምህርት ይጠይቃል—ቁ. 8።

መ. የእግዚአብሔርን ሕዝብ መልሶ ለማቀናበር፣ ዕዝራ በጣም ጠቃሚ ነበር፣ ምክንያቱም የሰማያዊውን እና የመለኮታዊውን ቅንብር እና ባሕል ጥቅል-ድምር የተሸከመ እና ሕዝቡ በእርሱ በኩል በእግዚአብሔር ቃል መልሶ መቀናበር የሚችሉበት ሰው ነበር—ቁ. 1-2።

ሠ. ሕዝቡ በመለኮታዊው ቃል ውስጥ ባሉ ሰማያዊ እውነቶች መልሰው ይማሩ እና መልሰው ይቀናበሩ ዘንድ ዕዝራ ወደ እግዚአብሔር ቃል መልሶ አመጣቸው።

ረ. የእግዚአብሔርን ሕዝብ መልሶ ለማቀናበር፣ ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ እና እግዚአብሔርን በሚገልጥ ቃል እነርሱን የማስተማር አስፈላጊነት ነበር—መዝ. 119፡2፣ 9፣ 105፣ 130፣ 140፦

1. የእግዚአብሔርን ሕዝብ መልሶ ማቀናበር በእግዚአብሔር ቃል ይሞሉ ዘንድ እነርሱን ወደ እግዚአብሔር ቃል ውስጥ በመጨመር ማስተማር ነው—ቆላ. 3፡16።
2. የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ሲሠራ፣ እግዚአብሔር ራሱ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ በኩል ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ከእግዚአብሔር ንጥረ-ነገር ጋር ወደ ማንነታችን ውስጥ ያድላል፤ በዚህ መንገድ መልሰን እንቀናበራለን—2 ጢሞ. 3፡16-17።

ሰ. በዕዝራ አገልግሎት በኩል መልሰው ከመቀናበራቸው የተነሣ፣ እስራኤል (በምሳሌ) እግዚአብሔርን የሚገልጥ ልዩ ሕዝብ፣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ እና የተለየ ሕዝብ ሆነ—ኢሳ. 49፡6፤ 60፡1-3፤ ዘካ. 4፡2፦

1. የተመለሱት ምርኮኞች የእግዚአብሔር ምስክር ለመሆን በግል እና በጋራ መልሰው ተቀናበሩ።

2. በእግዚአብሔር ኃሳብ እና እግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ተሰርጸው ነበር፤ ይህ የእግዚአብሔር ርቢ አደረጋቸው።
3. በእንደዚህ ዓይነት መለኮታዊ ቅንብር፣ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት እና በባሕርይ እግዚአብሔር ሆነ፤ ከዚህም የተነሣ፣ መለኮታዊውን ባሕርይ የሚገልጡ መለኮታዊ ሕዝብ ሆኑ—1 ጴጥ. 2፡9።

III. **በጌታ ምለሳ እግዚአብሔርን የሚገናኙ፣ በእግዚአብሔር ተሞልተው የረኩ፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆኑ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የተዋሐዱ፣ በእግዚአብሔር የተሞሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ የሚያውቁ ዕዝራዎች፣ ካህን አስተማሪዎች ያስፈልጉናል፤ በምለሳው ውስጥ አስተማሪ ለመሆን ብቁ የሆነው እንደዚህ ዓይነቱ ሰው ነው—ማቴ. 13፡52፤ 2 ቆሮ. 3፡5-6፤ 1 ጢሞ. 2፡7፤ 2 ጢሞ. 1፡11፡-**

ሀ. ጌታ ኢየሱስ ሕዝቡን ከሰይጣናዊው ጨለማ ወደ መለኮታዊው ብርሃን ሊያወጣቸው አስተማራቸው—ማር. 6፡6፤ ተዛ. ሐዋ. 26፡18፡-

1. ሰው ኃጢአት ውስጥ መውደቁ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት አቋረጠው፣ ይህም ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ለማወቅ እንዳይፈቅዱ አደረጋቸው፣ እንዲህ ያለው ለማወቅ ፈቃደኛ አለመሆን ጨለማን እና ሞትን አመጣ—ኤፌ. 4፡17-18።
2. ጌታ እንደ የዓለም ብርሃን በሞት ጥላ ለተቀመጡ ሕዝብ ለማብራት እንደ ታላቅ ብርሃን መጣ—ዮሐ. 8፡12፤ ማቴ. 4፡12-16።
3. በሞት እና በጨለማ የነበሩት የሕይወት ብርሃን ይቀበሉ ዘንድ የጌታ ትምህርት የብርሃን ቃልን ለቀቀ—ዮሐ. 1፡4።

ለ. ትምህርት የመጋረጃ መከፈት ከሆነው ከመገለጥ ጋር እኩል ነው—1 ጢሞ. 2፡7፤ ኤፌ. 3፡3-4፣ 9፡-

1. ማስተማር መጋረጃውን ማንሣት ነው፤ ሌሎችን ስናስተምር ከሥስታንዱ አምላክ የሆነ ነገር ማየት ይችሉ ዘንድ መጋረጃውን እያስወገድን መሆን አለበት።
2. በቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ውስጥ የሆነ ነገር ስንናገር፣ ንግግራችን መጋረጃውን ማንሣት መሆን አለበት፤ ይህ ማለት ትምህርታችን መገለጥን ማቅረብ አለበት—1 ጢሞ. 4፡6።
3. የዛሬዎቹ ዕዝራዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ምስክር፣ ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡ ይሆኑ ዘንድ እነርሱን እውነትን በማስተማር ለማቀናበር መድከም አለባቸው—ነህ. 8፡1-8፣ 13፤ 2 ጢሞ. 2፡2፣ 15፤ 1 ጢሞ. 3፡15።

ሐ. ምለሳው ከፍተኛው እውነት—ባለፉት ክፍለ ዘመናት የተመለሱት እውነቶች መጠናቀቅ—አለው—2፡4፤ 2 ጢሞ. 2፡2፣ 15፡-

1. መሟላት ያለበት ታላቁ ፍላጎት ምለሳውን ለማስቀጠል በጌታ ምለሳ ያሉ ቅዱሳንን ወደ እውነቱ ማምጣት ነው—1 ጢሞ. 2፡4፤ 2 ጢሞ. 2፡2፣ 15።
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ውጫዊዎቹ እውነቶች እና ውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች አሉን—ሉቃ. 24፡39፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 8፡34፣ 10፤ ቆላ. 3፡1፤ 1፡27።
3. መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና፣ ለ"ቅርንጫፎቹ" ትኩረት መስጠት ብቻ ሳይሆን ወደ "ሥሮቹ" እና "ግንዱ" በጥልቀት መግባት አለብን።
4. የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ደረጃዎች እና የክርስቶስን አካል ንጥር ትርጉሞች ማየት ያስፈልገናል—ዮሐ. 1፡14፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡4-6።

መ. በእውነት መቀናበር ውስጠ-መሠረታዊ ማንነታችን፣ ሕይወታዊ ቅንብራችን ለመሆን እውነቱ ውስጣችን መሥራቱ ነው—2 ዮሐ. 2፡-

1. የመለኮታዊው መገለጥ ውስጠ-መሠረታዊው ንጥረ-ነገር ወደ ማንነታችን ውስጥ መሥራት እና መቀናበር አለበት—ቆላ. 3፡6።
2. በመረዳታችን በኩል እውነቱ ወደ ውስጣችን ከገባ፣ በትውስታ ማኅደራችን ውስጥ ይቆያል፣ ከዚያም እውነቱን በትውስታ ማኅደራችን ውስጥ እናቆየዋለን፣ ይህም የእውነት ክምችት እንዲኖረን ያደርገናል—1 ጴጥ. 1፡13፤ 2 ጴጥ. 1፡15፤ 3፡1።
3. እውነቱ ወደ ትውስታ ማኅደራችን ከገባ በኋላ፣ ቋሚ እና የረጅም ጊዜ ምግብ ይሆናል፤ ከዚያም የእውነት ክምችት አለን፣ ቋሚ በሆነም ምግብ ሥር ነን—ቆላ. 3፡16፣ 4፤ 1 ጢሞ. 4፡6።

ሠ. በጌታ ምለሳ ያሉ ቅዱሳን በሙሉ በመለኮታዊው መገለጥ መሰልጠን አለባቸው—2 ጢሞ. 2፡2፣ 15፡-

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ወሳኝ መገለጦች ሁሉም ማለት ይቻላል በወንድም ኒ እና ወንድም ሊ አገልግሎት ተሸፍነዋል፤ ትኩረታችንን በእነዚህ ንጹሕ እና ጤናማ ነገሮች ላይ ማድረግ እንጂ “መርዛማ ቅሎች”ን በመሰብሰብ ጊዜያችንን ማባከን የለብንም—2 ነገ. 4፥38-41።
2. የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ለማየት ሁላችንም በሕይወት-ጥናቶች እና በሪካቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ ከግርጌ ማስታወሻዎቹ ጋር እርዳታ ማግኘት ያስፈልገናል—ነህ. 8፥8፣ 13።

© 2022 Living Stream Ministry